# አግላይ የምርጫ ሥርዓት እና ‹አውራ ፓርቲ›

April 13, 2018

አግላይ የምርጫ ሥርዓት እና ‹አውራ ፓርቲ›

ተሾመ ተስፋዬ( የሕግ ባለሙያ)

***

በአገራችን በ 2007 በተደረገው ምርጫ በርካቶችን ባስገረመ ሁኔታ ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ መቶ በመቶ ማሸነፉን ማወጁ ይታወቃል። ሆኖም ድርጅቱ ድሉን ባበሰረ ማግስት ሰፊ ሕዝባዊ ተቃውሞና አመፅ ገጥሞታል፡፡ የሰው ሕይወትና ንበረት የወደመ ሲሆን ብዙዎችም ለእስር ተዳርገዋል፡፡ አገሪቱም በአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ሥር እየተዳደረች ትገኛለች፡፡ መንግሥት ምርጫውን መቶ በመቶ ባሸነፈ ማግስት ሰፊ ሕዝባዊ ተቃውሞን ማስተናገዱን መነሻ በማድረግ በርካቶች የምርጫውን ውጤት ብሎም የምርጫውን ሥርዓት አግባብነት ጥያቄ ውስጥ ለመክተት ተገደዋል፡፡ በዚህ አጭር ጽሑፍ የምርጫ ሥርዓቱ በተለይ የተቃዋሚ ዜጎችን ድምፅ ባዶ በማስቀረትና ገዢውን ፓርቲ ቅቡልነት ወደሌለው "አውራ ፓርቲነት" በማሳደግ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች በፓርላማ ውስጥ ውክልና እንዳይኖራቸውና በምርጫ ብሎም አጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓቱ ላይ ተስፋ እንዲቆርጡ በማድረግ አገሪቱን ዋጋ እያስከፈላት መሆኑን ለማሳየትና የማሻሻያ ሐሳብ ለማቅረብ ተሞክሯል።

የምርጫ ሥርዓት ሲባል በርካታ ጉዳዮችን የሚያካትት ቢሆንም ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ የመራጮች ድምፅ ወደ ፓርላማ ወንበር የሚቀየርበትን ሒደት የሚገልጽ ነው፡፡ የአገራችንን የምርጫ ሥርዓት በአግባቡ ለመረዳት እንዲያስችለን በዓለም የታወቁ ዋና ዋና የምርጫ ሥርዓቶችን በአጭሩ እንመልከት። የመጀመሪያው የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ሲሆን ‹first past the post› እና ‹absolute majority vote (50%+1)› የሚባሉትን ያካትታል። በ‹first past the post› የምርጫ ሥርዓት መሠረት አገሪቱ በምርጫ ክልሎች ትከፋፈልና በያንዳንዱ የምርጫ ክልል ከተሳተፉ ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫውን ድምፅ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ይሆናል። በ‹absolute majority› ሥርዓት ደግሞ አሸናፊው ተወዳዳሪ ከያንዳንዱ ተፎካካሪው የተሻለ ድምፅ ከማግኘት ባለፈ የአብዛኛውን መራጭ ሕዝብ (50%+1) ማግኘት ይጠበቅበታል። ኹለተኛው ደግሞ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት (proportional representation) በመባል ይታወቃል። በዚህ የምርጫ ሥርዓት ተወዳዳሪዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳንዳቸው ባገኙት አጠቃላይ ድምፅ መጠን ተመጣጣኝ ወንበር ያገኛሉ። ማለትም እያንዳንዱ ተወዳዳሪ የሚያገኘው ወንበር በአገሪቱ የሚገኙ መራጮች ከሰጡት ድምፅ ጋር የተመጣጠነ ነው።

በመሠረቱ በዓለም ላይ እየተተገበሩ ከሚገኙ የምርጫ ሥርዓቶች መካከል ምርጡ የትኛው ነው? በሚለው ላይ መግባባት የለም። ሁሉም የምርጫ ሥርዓቶች የየራሳቸው ጠቃሚና ጎጂ ገጽታ ሊኖራቸው ይችላል። ሆኖም የአንድን አገር አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታና ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለውን መርጦ መጠቀም እንደሚገባ ባለሙያዎች ይመክራሉ። በዚህም መሠረት አገሮች ከላይ ከተጠቀሱት ሥርዓቶች አንዱን በመምረጥ ወይም እንደሁኔታው ሁለቱን ሥርዓቶች እያዳቀሉ የምርጫ ሥርዓታቸውን ቀርጸው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

የምርጫ ሥርዓቱ አግላይነት

***

አገራችን ኢትዮጵያ የምትከተለው ‹first past the post› የሚባለውን የምርጫ ሥርዓት ነው። ይህ የምርጫ ሥርዓት በሕገ መንግሥቱ ደረጃ ዕውቅና ተሰጥቶት አንቀጽ 54 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ከሚገዛው የምርጫ ሕጉ አዋጅ ቁጥር 532/99 አንቀጽ 25 እና 49 (1) ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመረዳት እንደሚቻለው አገሪቱ ከ 550 ባልበለጠ የምርጫ ክልል የምትከፋፈል ሲሆን በያንዳንዱ የምርጫ ክልል ሊወዳደሩ ከሚችሉት ከ 12 ያልበለጡ ተወዳዳሪዎች መካከል

የበለጠ ድምፅ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ይሆናል። በዚሁ መሠረት አሸናፊው ከሌሎቹ ተወዳዳሪዎች የተሻለ ድምፅ ከማግኘት ባለፈ የአብዛኛውን መራጭ ድምጽ (50%+1) ማግኘት አይጠበቅበትም። በሌላ በኩል ለተቀሩት ተወዳዳሪዎች የተሰጠው ድምፅ በሙሉ የፓርላማ ውክልና ሳያገኝ ዋጋ አልባ ሆኖ ይቀራል።

ሕገ መንግሥቱን በማርቀቅና በማፅደቅ ሒደት አወዛጋቢ ከሆኑ ነጥቦች አንዱም የምርጫ ሥርዓቱ ጉዳይ ነበር። በወቅቱ በርካታ ምሁራንና ፖለቲከኞች ለኢትዮጵያ ተመራጩ የምርጫ ሥርዓት ሕገ መንግሥቱ ላይ የተካተተው ሳይሆን የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት የሚባለው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል። ክርክራቸውን ለመደገፍ የሚያቀርቡት ዋና ምክንያትም የተመጣጣኝ ክልና የምርጫ ሥርዓት ሁሉም ፓርቲዎች ባገኙት ድምፅ መጠን ወንበር የሚያገኙበት በመሆኑ የሚመሠረተው ፓርላማ የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ምርጫ የሚወክል ከመሆኑም በላይ ከፌደራል ሥርዓቱም ጋር ተጣጥሞ ይሄዳል የሚል ነው፡፡ ሆኖም ሕገ መንግሥቱን በማርቀቅም ሆነ በማፅደቅ ሒደት ወሳኙን ሚና የተጫወተው ገዢው ሐሳቡን ያልተቀበለው ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው አገሪቱ የ‹first past the post›ን የምርጫ ሥርዓት እንድትከተል በሕገ መንግሥት ደረጃ እንዲደነገግ አድርጓል፡፡ በወቅቱ በገዢው ፓርቲ ባለሥልጣናትና ፖሊሲ ቀራጮች በኩል የቀረበው ምክንያት የምርጫ ሥርዓቱ መንግሥት ለማደራጀትም ሆነ የመንግሥትን ሥራ ለማከናወን ቀላል ነው፡፡ አገሪቱም ገና ከእርስ በእርስ ጦርነት የተላቀቀችና በኢኮኖሚ የደቀቀች በመሆና የተደቀኑብንን በርካታ ችግሮች ለመፍታት የሚችል ጠንካራ መንግሥት ለመመሥረት ያስችለናል፡፡ በአንጻሩ የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት ውስብስብና ድርድርን የሚጠይቅ ስለሆነ ኋላቀር ከሆነው የፖለቲካ ባህላችን አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ይከብደናል የሚል ነው፡፡

በእርግጥ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የተመረጠልን የምርጫ ሥርዓት ጠንካራና ፖሊሲዎችን በቀላሉ ለመተገበር የሚችል መንግሥት ለመፍጠር የሚረዳ መሆኑ ይታመናል፡፡ ነገር ግን በርካቶች በገዢው ፓርቲ የቀረበውን ምክንያት ከመነሻው በጥርጣሬ ነው የተመለከቱት፡፡ ለዚህም ኹለት መሠረታዊ ምክንያቶችን ያነሳሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያታቸው ገዢው ፓርቲ ያነሳቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ባህል ኋላቀርነት ችግሮች በሒደት የሚፈቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ወደ ፊት በቀላሉ ለማሻሻል በሚያስችል መልኩ በአዋጅ ደረጃ መደንገግ ሲገባው በመቃብሬ ላይ ካልሆነ አይሻሻልም በሚለው ሕገ መንግሥት ላይ ማስፈር አልነበረበትም የሚል ነው፡፡ ኹለተኛው ምክንያት ከዓመታት በኋላ አገሪቱ በኢኮኖሚ አደገች፣ ዴሞክራሲም አበበ እያለ በሚለፍፍበት ሁኔታ እንኳን ገዢው ፓርቲ የምርጫ ሥርዓቱን ለማሻሻል አንዳችም ጥረት አላደረገም፡፡ ይልቁንም የምርጫ ሥርዓቱን የመረጠውና ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ያካተተው ከመነሻው የነበረውን ድርጅታዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት በመጠቀም የተከፋፈሉና አቅማቸው የተዳከመ ተቃዋሚዎች በመታጀብ ምርጫ እያደረገ በቀላሉ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ስለሚያስችለው ነው የሚል ነው፡፡

በዚህም የተነሳ በሕገ መንግሥት ደረጃ ከፀደቀም በኋላ የተለያዩ አካላት በተለይም ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ሥርዓቱ እንዲሻሻል ግፊት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም በመንግሥትም ሆነ በገዢው ፓርቲ በኩል ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በዚህ ረገድ አቶ በረከት ስምኦን የ 2002 ቱን ምርጫ ውጤት ማግስት "የሁለት ምርጫዎች ወግ ናዳን የገታ አገራዊ ሩጫ" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ ስለ ጉዳዩ ያሰፈሩትን መመልከቱ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አቶ በረከት በመጽሐፋቸው ላይ የ 1997 ቱ ምርጫን እንከን የለሽ ለማድርግ ኢሕአዴግ ከተቃዋሚዎች ጋር ድርድር በሚያደርግበት ወቅት የምርጫ ሥርዓቱ ወደ ተመጣጣኝ የውክልና ሥርዓት እንዲቀየር በኢዴፓ መድኅንና በኅብረት ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ መደረጉን ይገልጻሉ፡፡ በመጽሐፋቸው ገጽ 57 ላይም የምንከተለው የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት መሆኑን ከጠቀሱ በኋላ ስለ ሥርዓቱ ሲያብራሩ "በአብላጫ ድምጽ ላይ የተመሠረተ የምርጫ ሥርዓት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ወይም እጩዎች መካከል፤ የመራጩን ሕዝብ አብላጫ ድምጽ ያገኘ ወገን ሕዝቡን ወክሎ ወደ ምክር ቤት የሚገባበት ነው፡፡ በውድድሩ አናሳውን የመራጭ ድምጽ ያገኙት ደግሞ ተሸናፊዎች በመሆናቸው ለምክር ቤት አባልነት የማይበቁበት የምርጫ ሥርዓት ነው፡፡" በማለት ገልጸዋል፡፡

የአቶ በረከት አገላለጽ በተለይም ሰረዝ የተደረገበት አገላለጻቸው በጥንቃቄ ካልተነበበ በስተቀር ስለምርጫ ሥርዓቱ የተዛባ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚችል ነው፡፡ በመነሻችን ላይ እንደተመለከተው በግርድፉ (በጥቅሉ) ሲታይ የኛ የምርጫ ሥርዓት በአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ምድብ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ዓይነት የምርጫ ሥርዓቶች አሉ፡፡ አንደኛው ‹absolute majority vote (50%+1)› በመባል የሚታወቀው ሲሆን ከስያሜው ለመገንዘብ እንደሚቻለው ለመመረጥ ተወዳዳሪው ከመራጩ ሕዝብ የአብላጫውን ድምጽ ማለትም 50 ከመቶ በላይ ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ እኛ የምንከተለው ግን ‹first past the post› በመባል የሚታወቀውን ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት አሸናፊው የሚጠበቅበት ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የበለጠ ድምጽ ማግኘት ብቻ ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱም ቃል በቃል አንቀጽ 54/2 ላይ

"ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበት" በማለት ይገልጸዋል፡፡ የምርጫ ሕጉም ቢሆን ተወዳዳሪ የሚለውን እጩ በሚል ከመተካቱ በስተቀር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡ ውድድሩ በእጩዎች መካከል ነው እንጂ የመራጩን ሕዝብ አብላጫ ድምጽ የማግኘት ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ባለሙያዎች ይኽን የምርጫ ሥርዓት የአርተፊሻል አብለጫ ድምጽ (artificial majority) ሥርዓት በማለት የሚገልጹት፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የአቶ በረከት "የመራጩን ሕዝብ አብላጫ ድምጽ ያገኘ" የሚለው አገላለጽ የምርጫ ሥርዓቱን ‹absolute majority vote (50%+1)› በመባል ከሚታወቀው ጋር ሊያመሳስለው ስለሚችል በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡ ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመጣ አቶ በረከት በመጻፋቸው ላይ ኢሕአዴግ የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የተሻለ መሆኑን ስለሚያምን የማሻሻያ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን ከመግለጽ ባለፈ የሚሻልበትን ምክንያት በግልጽ አላስቀመጡም፡፡

አርተፊሻል አብላጫ ድምጽና ያልተወከሉ የምርጫ ካርዶች

***

ገዢው ፓርቲ የምርጫ ሥርዓቱ ለአገራችን የተሻለ መሆኑን ቢገልጽም በንድፈ ሐሳብ ደረጃም ሆነ በተግባር ሲታይ ሥርዓቱ በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ለመገንዘብ አይከብድም፡፡ የምርጫ ሥርዓቱ አንዱ ችግር አርቲፊሻል አብላጫ ድምፅ የሚፈጥር መሆኑ ነው። ከላይ እደተገለጸው ገዢው ፓርቲ ለማሸነፍ በየምርጫ ክልሉ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የበለጠ ድምፅ ማግኘት እንጂ የመራጮችን አብላጫ ድምፅ ማግኘት አይጠበቅበትም። በአንድ የምርጫ ክልል ደግሞ እስከ 12 ፓርቲዎች ወይም ግለሰቦች ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ በሚደረግ ምርጫ ለእያንዳንዱ ተወዳዳሪ የሚሰጠው ድምፅ ከገዢው ፓርቲ ያነሰ ቢሆንም ሌሎች ተወዳዳሪዎች የሚያገኙት ድምጽ በድምሩ ሲታይ ከገዢው ፓርቲ የበለጠ ሊሆን የሚችልበት አገጣሚ ሰፊ ነው። ማለትም ገዢው ፓርቲ መንግሥት ቢመሠርት እንኳን የግድ አብዛኛው ሰው ይደግፈዋል ማለት አይደለም። ከ 50 በመቶ በታች ድምፅ አግኝቶ እንኳን ሊያሸንፍና መንግሥት ሊመሠርት ይችላል። ሌላው መሠረታዊ ችግር ደግሞ በየምርጫ ክልል ተሸናፊዎቹን ተወዳዳሪዎች የመረጡ መራጮችን ድምፅ ሙሉ በሙሉ ዋጋ አልባ አድርጎ ማስቀረቱ ነው፡፡ ምክንያቱም የምርጫ ሥርዓቱ አሸናፊ ሁሉን የሚያገኝበት ተሸናፊው ደግሞ ምንም የማያገኝበት ነው።

በአገራችን ያለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች አወቃቀርና እንቅስቃሴ ላይ የሚስተዋለው ችግር ሲታከልበት ደግሞ የምርጫ ሥርዓቱ የሚያስከትለውን ጉዳት የከፋ ያደርገዋል፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የምርጫ ሥርዓቱ ባለበት ሁኔታ እንኳን በተሻለ ለመተግበር እንዲቻል ከኹለትና ሦስት ያለበለጡ ጠንካራ ፓርቲዎች መኖርን ግድ ይላል፡፡ ይኽም ተቃዋሚዎች ከገዢው ጋር ጠንካራ ፉክክር ለማድረግ እንዲችሉና የመራጮች ድምጽ ተበታትኖ እንዳይቀር በማድረግ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታውን ያግዛል፡፡ ነገር ነባራዊ እውነታው ሲታይ ታቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙና የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በተለይም ኅብረ ብሔር የፖለቲካ ፓርቲዎቸ እንቅስቃሴያቸውም ሆነ ደጋፊያቸው በአብዛኛው በከተሞች አከባቢ የተወሰነ ሲሆን የሚያገኙት ድምፅም በየምርጫ ክልሉ የተበታተነ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ገዢውን ፓርቲ ከማጀብ ባለፈ የማሸነፍ ዕድላቸው ጠባብ ነው። በተጨባጭም ሲታይ አገሪቱ እስካሁን ካደረገቻቸው አምስት ምርጫዎች ከ 97 ቱ ምርጫ ውጪ ተቃዋሚዎች የረባ የፓርላማ ወንበር አግኝተው አያውቁም፡፡ በባለፉት ኹለት ተከታታይ ምርጫዎች ደግሞ ገዢው ፓርቲ በ 2002 99.6 በ 2007 ደግሞ መቶ በመቶ በማሸነፍ የመደብለ ፓርቲ ሥርዓቱ ያከተመለት ይመስላል፡፡

ተቃዋሚዎችና ሂደቱን የታዘቡ የተለያዩ ተቋማት እስካሁን በተደረጉት ምርጫዎች ገዢው ፓርቲ አሸናፊ ሆኖ የወጣው ግልጽና ስውር ጫናዎችን በማሳደር መሆኑን ገልጸው ይተቻሉ፡፡ ይኽ በራሱ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳያችን ሳንወጣ ገዢው ፓርቲ በተለይም በባለፉት ኹለት ምርጫዎች ላገኘው የተጋነነ ውጤትና ተቃዋሚዎች ወንበር ለማጣታቸው የምርጫ ሥርዓቱ አስተዋጽዖ ምንድን ነው? የተመጣጣኝ የውክልና ሥርዓትን ብንከተልስ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር? የሚለው ነጥብ በደንብ መታየት አለበት፡፡ የምንከተለው የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓትን ቢሆን ኖሮ ምርጫ ቦርዱ ባረጋገጠው ውጤት መሠረት እንኳን ተቃዋሚዎች በርካታ የፓርላማ ወንበሮችን ማግኘት ይችሉ እንደነበርና ገዢው ፓርቲም ያገኘውን ውጤት ያህል ላያገኝ እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ለምሳሌ ምርጫ 2002 ትን እንመልከት፡፡ እንደሚታወቀው ምርጫው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ 547 የምርጫ ወርዳ ተከፍሎ ተካሂዷል፡፡ ገዢው ፓርቲና አጋር ድርጅቶቹ 99.6 በመቶ ውክልና አግኝተዋል፡፡ ሆኖም የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓትን ብንከተል ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን እንደነበር ለመረዳት ኢዮብ አምዴ የተባሉ አጥኚ ‹The Impact of Electoral System on Political Representation in Diversified Society: An appraisal of National

Elections of Ethiopia› በሚል ርእስ ያቀረቡትን ጥናታዊ ጽሑፍ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ አጥኚው የምርጫ ቦርድ ውጤት ላይ ተመሥርተው በቁጥር የተደገፈ ግኝት አቅርበዋል፡፡ የምንከተለው የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓትን ቢሆን ኖሮ የሚኖረውን ልዩነት የአዲስ አበባን እና አጠቃላይ አገር ዐቀፍ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ውጤትን መሠረት በማድረግ አሳይተዋል፡፡ የአዲስ አበባውን በተመለከተ ኢሕአዴግ ለከተማው ከተመደበው 23 የምርጫ ወንበር 22ን ያሸነፈ ቢሆንም ከአጠቃላይ የመራጮች ድምጽ ያገኘው ድምጽ 49.38 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት ብንከተል ኖሮ 11 ወንበር ብቻ ሲያገኝ የተቀረው የተቃዋሚዎች ድርሻ ይሆን ነበር፡፡ በአገር ዐቀፍ ደረጃ ሲታይ ከአጠቃላይ 547 ወንበር ውስጥ ኢሕአዴግ ያገኝ የነበረው 270 ወንበር ብቻ ሲሆን የተቀረው 277 ወንበር ለተቃዋሚዎችና ለአጋር ድርጅቶች የሚከፋፈል ነበር፡፡ በሌላ በኩል አጠቃላይ ከመረጠው 30,181,686 ሕዝብ ውስጥ 15,277,970 (50.6 በመቶ) ድምጾች ውክልና ሳያገኙ ባክነው ቀርተዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት አጥኚው በደረሱበት ድምዳሜ በአገር ዐቀፍ ደረጃ ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚዎች ያገኙት አጠቃላይ የድምጽ ውጤት ብዙ ልዩነት ባይኖረውም ለገዢው ፓርቲ የተጋነነ ውጤት የምርጫ ሥርዓቱ ያለው አስተዋጽዖ የጎላ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የ2007ቱን በምርጫው ኢሕአዴግ ከአጋር ድርጅቶች ጋር ሆኖ መቶ በመቶ አሸንፏል። ይኽን እንዳለ ብንቀበል እንኳን ገዢው ፓርቲ የሚያደርስባቸውን ግልጽና ስውር ተጽዕኖ ተቋቁመው በርካታ ዜጎች ተቃዋሚዎችን መምረጣቸው ይታወቃል። የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓትን ብንከተል የእነዚህ ዜጎች ድምፅ በዚያው ልክ የፓርላማ ውክልና ያገኝ እንደነበር። ነገር ግን በምርጫ ሥርዓታችን አግላይነት የተነሳ አንድም ወንበር ሊያስገኙ አልቻሉም። ገዢውን ፓርቲ የመረጡት ድምፆች ወደ ፓርላማ ወንበርነት ሲቀየሩ የተቃዋሚዎች ድምፅ የተበታተነ በመሆኑ ብቻ የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ከመጣል ያለፈ ሚና አልነበረውም። በመሆኑም የምርጫ ሥርዓቱ ገዢውን ፓርቲ ወደ አርቲፊሻል አውራ ፓርቲነት ያሳደገ ሲሆን የሌሎች መራጮችን ድምጽ ደግሞ ውክልና በማሳጣት ፓርላማው በአንድ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሞላ አድርጓል፡፡

ቀጣዩ ፈተና

***

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የምርጫ ሥርዓቱ አግላይ በመሆኑ ለአገራችን ተመራጭ አይደለም፡፡ ተቃዋሚዎችና ባለሙያዎች የምርጫ ሥርዓቱ እንዲለወጥ ከመነሻው ጀምሮ አጥብቀው ሲከራከሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ገዢው ፓርቲ ከምርጫ ሕጉ ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች ላይ እንጂ የምርጫ ሥርዓቱን በተመለከተ ለመደራደርም ሆነ ለማሻሻል ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የምርጫ ሥርዓቱ ለአገራችን ተመራጭ ባይሆንም ጉዳቶቹን ለመቀነስና ባለበት ሁኔታ በአገሪቱ የዴሞክራሲ ሥርዓትን በተሻለ ሁኔታ እንዲያሰፍን ከተፈለገ በርካታ ሁኔታዎች ሊሟሉ እንደሚገባ ይመከራል፡፡ እንደ ባለሙያዎች ምክር ከኹለትና ሦስት የማይበልጡ ጠንካራና ልዩነታቸውም ጠባብ የሆነ ፓርቲዎች ሊኖሩ ይገባል። ይኽም የተቃዋሚዎች ድምጽ ሳይበታተን፣ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡና ጠንካራ ተፎካካሪ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ ነገር ግን በተቃዋሚዎቹ በራሳቸው ችግርና መንግሥትም በሚደርስባቸው ግልጽና ስውር ጫና ምክንያት እውን ሊሆን አልቻለም፡፡ በተጨማሪም ጠነካራና ነጻ የሆነ ፍርድ ቤት፣ ነጻ የሲቪክ ማኅበራትና ሚዲያ ሊኖሩ ይገባል። ነገር ግን ገዢው ፓርቲ ለዚህ ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር ይልቅ በተለይም ምርጫ 97ትን ተከትሉ ባወጣቸው አፋኝ ሕጎችና አተገባበር የተዳከሙ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሚመሠረተው ፓርላማ ጠንካራና አስፈጻሚውን በአግባቡ የሚቆጣጠር መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሠረቱ የፓርላማ አባላት የሕዝብ ተወካይ እንደመሆናቸው ለአገሪቱና ለሕዝቡ አጠቃላይ (ላልመረጧቸውም ጭምር) ጥቅም መሥራት እንዳለባቸው ይታመናል። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 54/4/5 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የምክር ቤቱ አባላት ተገዢነታቸው ለሕገ መንግሥቱ፣ ለሕዝብና ለኅሊናቸው ሲሆን በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጡት ድምፅም ሆነ አስተያየት ምክንያት ተጠያቂነት እንደሌለባቸው ተደንግጓል። ሆኖም የኢሕአዴግ የፓርላማ አባላት ድርጅቱ በሚከተለው የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የፖለቲካ ዲሲፕሊን የተጠረነፉ በመሆኑ የሕዝቡን ፍላጎት ለማስተጋባትና የአስፈጻሚውን አካል ለመቆጣጠር አቅም የላቸውም። በፓርቲው አሠራር መሠረት አብዛኛው ነገር አስቀድሞ በፓርቲው የሚወሰን በመሆኑና አባላቱም ይኽን የማስፈፀም ግዴታ ስላለባቸው ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ ለሕዝብ ሲቆሙ እምብዛም አይታይም። በአንጻሩ ገዢው ፓርቲ ፓርላማው በአባላቱ መሞላቱን በመጠቀም የፓርቲውን ፖሊሲ ያለ ተቀናቃኝ ለመተግበርና የተለያዩ አፋኝ ሕጎችን በማውጣት ሥልጣኑን ወደማደላደልና ተቃውሞን ለማፈን እንዳዋለው ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

ከላይ የተገለጹት ሁኔታዎች ቢሟሉ ኖሮ ባለበት ሁኔታም ቢሆን የተለያዩ ፓርቲዎች የመወከል ዕድላቸው የሰፋ ይሆን ነበር፤ ገዢው ፓርቲም ወደ ጠቅላይ ፓርቲነት ያደረገው ጉዞ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይገታ ነበር፤ የዜጎች መብትም በተሻለ ሁኔታ በተከበረ ነበር፡፡ ሆኖም ገዢው ፓርቲ የምርጫ ሥርዓቱ በፈጠረለት አመቺ ሁኔታ በየወቅቱ በሚያገኘው አርቲፊሻል አብላጫ ድምፅ መሠረት በማድረግ "አውራ ፓርቲ" መሆኑን በማወጅ ሰፊ የሕዝብ ተቀባይነት አለኝ ወደሚል መታበይ ውስጥ ገብቷል። ለተቃውሞ ድምፆችም ተገቢውን ትኩረትና ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ወደማፈን ተግባሩ አዘንብሏል። ይኸም በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ገዢውን ፓርቲ የማይደግፉት የመገለል ስሜት እንዲሰማቸው አድርጓል፡፡ በዚህም የተነሳ በምርጫ ሥርዓቱ ብሎም በአጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓቱ ላይ ተስፋ እንዲቆርጡ ሆኗል፡፡ አገራችንንም በርካታ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡ ወደፊትም መፍትሔ ካልተበጀለት የሚያስከትለው አደጋ የከፋ ነው፡፡

በመሆኑም በገዢው ፓርቲ በኩል የምርጫ ሥርዓቱን ላለማሻሻል ሲቀርብ የነበረው መከራከርያ ብዙም የሚያስኬድ አይመስልም፡፡ በእርግጥም መንግሥት ሕዝባዊ ተቃውሞውን ተከትሎ የምርጫ ሕጉን ለማሻሻል ቃል ገብታል፡፡ ማሻሻሉ እንደከዚህ ቀደሙ ሌሎች ዝርዝር የምርጫ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከት ይኹን ወይስ የምርጫ ሥርዓቱን እስከማሻሻል የሚዘልቅ ለመሆኑ በግልጽ ይፋ አልሆነም፡፡ ተቃዋሚዎችም ከገዢው ጋር እያደረጉት ባለው ድርድር ለምርጫ ሥርዓቱ መሻሻል ትልቅ ትኩረት ሊሰጡ የሚገባ ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የምርጫ ሥርዓቱ በሕገ መንግሥት ደረጃ የተደነገገ ከመሆኑ አንጻር ማሻሻሉ የሕገ መንግሥቱን መሻሻል የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም አገሪቱ ካለችበት አሳሳቢ ሁኔታ አንጻር ገዢው ፓርቲ ለዚህ እራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

